# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የቦታ ርቀት ትና የጊዜ እጥረት ያልገደበው የአቅም ግንባታ

ኢያሱ መሰለ

ሰላም እንደምን ሰነበታችሁ የአምዳችን አንባቢዎች! ባለፈው ሳምንት ዝግጅታችን አቶ ቴዎድሮስ በቀለ የመልካ ዋከና የውሃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ሥራ አስኪያጅ ስለጣቢያው ታሪካዊ ዳራ እና አሁን ስለሚገኝበት ቁመና የሰጡንን መረጃ ማስነበባችን ይታወሳል።

በዛሬው ዝግጅታችን ደግሞ በ2004 ዓ.ም ብልሽት አጋጥሞት ከሥራ ውጭ የሆነውን ማሽን ወደ ስራ ለማስገባት እየተደረገ ያለውን ጥረት እንዲሁም በአጫጭር የሥራ ላይ ስልጠናዎች እና በዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስር የጣቢያውን ሠራተኞች አቅም ለመገንባት የተከናወኑ ሥራዎችን በተመለከተ አቶ ቴዎድሮስ የሰጡንን መረጃ እናስነብባችኋለን።

እንደሚታወቀው የመልካ ዋከና የውሃ ኃይል ማመንጫ የተገነባው ከ37 ዓመታት በፊት በመሆኑ በራስ ኃይል የጥገና ሥራዎችን ለመስራት የሚያስችሉ የመለዋወጫ እቃዎች አለመገኘት በጥገና ሥራው ላይ ፈተና እንደሆነ ባለፈው ጊዜ ጠቅሰውልን ነበር። በዚህም ምክንያት በ2004 ዓ.ም ችግር አጋጥሞት ከስራ ውጭ የሆነውን አንዱን ዩኒት ወደ ስራ ለማስገባት በተቋሙ ሰራተኞች ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ ቢቆይም አሁንም ድረስ ወደ ሥራ ማስገባት ባለመቻሉ ጣቢያው በሶስቱ ዩኒቶች ብቻ 90 ሜጋ ዋት እያመረተ እዚህ ድረስ ለመዝለቅ ተገድዷል።

በተያዘው በጀት ዓመት ግን የተለያዩ አማራጮችን ሁሉ በመጠቀም የተበላሸውን ማሽን ወደ ሥራ ለማስገባት እቅድ መያዙን አቶ ቴዎድሮስ ተናግረዋል። በዚሁ መሰረት የኢትዮጵያ መንግሥት ኃይል ማመንጫውን ከገነባው ከሩሲያ መንግሥት ጋር በመነጋገር በበጀት ዓመቱ ማሽኑን ወደ ሥራ ለማስገባት እየሠራ ይገኛል። ከጥቅምት 25 2017 ዓ.ም ጀምሮ የሩሲያ ባለሙያዎች በቦታው ተገኝተው የኢንስፔክሽንና መረጃ የመሰብሰብ ሥራ በመሥራት



አቶ ቴዎድሮስ በቀለ

ለመልሶ ግንባታ ሥራው ውል ፈጽመው ወደ ሥራ የሚገቡ ይሆናል ብለዋልም።

ለኢንዱስትሪዎች መስፋፋት፣ ማበብና እና ምርታማነት ጉልህ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ የኢነርጂ ዘርፎች መካከል ኤሌክትሪክ ግንባር ቀደም ነው። የኢነርጂው ዘርፍ ራሱን የቻለ ትልቅ ኢንዱስትሪ ከመሆንም ባለፈ ለተለያዩ ኢንዱስትሪዎች የህልውናቸው መሠረት የመሆኑ ጉዳይ አጠያያቂ አይሆንም። የማኑፋክቸሪንግ፣ የትራንስፖርት፣ የቴሌኮም፣ የሆቴሎች ኢንዱስትሪ እና ሌሎችም ምሉዕነታቸው የሚረጋገጠው የኢነርጂው እንዱስትሪ በሚሰጣቸው ዋስትና ነው። ከዚህ አንጻር የኢነርጂው ኢንዱስትሪ የተለያዩ ኢንዱስትሪዎችን ይወልዳልም፤ ያዋልዳልም ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ዩኒቨርሲቲዎች የኢንዱስትሪውን የሰው ኃይል አቅም ለመግንባት፤ ኢንዱስትሪዎችም ዩኒቨርሲቲዎች በንድፈ-ሀሳብ ደረጃ የሚሰጡትን ትምህርት እንደ ቤተ ሙከራ ሆነው በተጨባጭ ለማሳየት ወይም አንዳቸው የአንዳቸውን ክፍተት ለመሙላት ትስስር ፈጥረው መጓዝ እንዳለባቸውም ይታመናል። ከዚህ አንጻርም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ካለፉት ቅርብ ዓመታት ወዲህ ለትምህርት ምቹ ባልሆኑና ከከተሞች ርቀው በሚገኙ ኃይል ማመንጫና ማከፋፈያ ጣቢያዎቹ ለሚገኙት ሠራተኞቹ በዩኒቨርሲቲ- ኢንዱስትሪ ትስስርና በአጫጭር የሥራ ላይ ሥልጠናዎች የሙያተኞቹን አቅም እየገነባ ይገኛል።

አቶ ቴዎድሮስ እንደሚያስረዱት፤ ጣቢያው ከመደ ወላቡ ዩኒቨርሲቲና ከበቆጂ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ጋር ትስስር በመፍጠር ለሰራተኞቹ የትምህርት እድል አመቻችቷል። በመጀመሪያው የትምህርት ፕሮግራም 21 የሚሆኑ የተቋሙ ሠራተኞችን ከሙያቸው ጋር በተገናኘ በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች በመጀመሪያ ዲግሪ አስመርቋል። 12ኛ ክፍል ጨርሰው በአቅም ማነስ ምክንያት ወደ ሌላ ቦታ በመሄድ ዩኒቨርሲቲ ገብተው መማር ያልቻሉ የአካባቢው ነዋሪዎች እንዲሁም በኢትዮ ቴሌኮም እና በኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚሰሩ ሌሎች ሰባት ሰዎችም ጣቢያው ለሠራተኞቹ ያመቻቸውን የትምህርት እድል እንደ ጥሩ አጋጣሚ ተጠቅመው ከጣቢያው ሠራተኞች ጋር በመጀመሪያ ዲግሪ ለመመረቅ በቅተዋል።

በሁለተኛው ዙር የትምህርት መርሃ-ግብር ደግሞ ቁጥራቸው ከ40 እስከ 50 የሚሆኑ የጣቢያው ሠራተኞችና የአካባቢው ነዋሪዎች የሌቭል አራት እና የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርታቸውን በመማር ላይ እንደሚገኙ ጠቅሰዋል። ጣቢያው ከዩኒቨርሲቲዎች ለሚመጡ መምህራን በየሳምንቱ ቅዳሜና እሁድ የትራንስፖርት አገልግሎት እና የማረፊያ ቦታ በማመቻቸት የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዲቀላጠፍ ያደርጋል። ለስልጠናው የሚያስፈልጉ የመማሪያ ክፍሎችንና ቁሳቁሶችንም ያሟላልም ብለዋል።

የጣቢያው ሰራተኞች በሶስት ሺፍት ተከፋፍለው 24 ሰዓት እንደሚሠሩ የተናገሩት አቶ ቴዎድሮስ፤ በትምህርት ላይ የሚገኙ ሠራተኞች ቅዳሜና እሁድ ከስራ ውጭ ሆነው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ የሥራ ኃላፊዎችን ጨምሮ ሌሎች ሠራተኞች ቦታቸውን እንዲሸፍኑላቸው ይደረጋል። የሰው ኃይል እጥረት ተከስቶ ተማሪዎቹ በሥራ ገበታቸው ላይ እንዲገኙ የሚያስገድድ ነገር ከተፈጠረ ደግሞ የማካካሻ ትምህርት እንዲያገኙ እንደሚመቻችም አስረድተዋል።

በጣቢያው የተሻለ ልምድ ያካበቱ ነባር ሙያተኞችም ለአዳዲስና በመማር ላይ ላሉት የጣቢያው ሠራተኞች አጫጭር የሥራ ላይ ስልጠና የመስጠትና ልምዳቸውን እና እውቀታቸውን የማካፈል ሥራ እንደሚሠሩ ተናግረዋል። የተግባር ትምህርት ለማግኘት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋሟቱ ለሚመጡ የበቆጂ ቴክኒክና ሙያ እንዲሁም የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ መደበኛ ተማሪዎችም እንዲሁ የተማሩትን የንድፈ ሀሳብ ትምህርት በተግባር መደገፍ እንዲችሉ የጣቢያው ነባር መሃንዲሶችና የተሻለ እውቀት ያላቸው ባለሙያዎች አጫጭር ገላጻና ማብራሪያ እንደሚያደርጉላቸው ሥራ አስኪያጁ ገልጸዋል።

ጣቢያው የትምህርት እድል ማመቻቸቱ በርካታ ጥቅሞች እንዳሉት የተናገሩት ሥራ አስኪያጁ፤ ከእነዚህ ውስጥ ሠራተኞች ለትምህርት ካላቸው ፍላጎት አንጻር ዝውውር በመጠየቅ ጊዜያቸውን እንዳያጠፉና ሥራ ጥለው እንዳይሄዱ ያደርጋቸዋል። በተለይም ተቋሙ ከቴክኒክና ሙያ በሌቭል የቀጠራቸው ሠራተኞች አቅማቸውን በኢንጂነር ደረጃ አሳድገውና ያሉባቸውን ክፍተቶች ሞልተው ለተሻለ አፈጻጸም እንዲዘጋጁ ያስችላቸዋል ብለዋል።

እንደ አቶ ቴዎድሮስ ማብራሪያ፤ ለጣቢያው ሠራተኞች የትምህርት እድል መመቻቸቱ ምቹ የሥራ ቦታን በመፍጠር ሥራና ሠራተኛው ተጣጥመው እንዲሄዱ የማድርግና ሠራተኛው ደስ እያለው ሥራውን እንዲሠራ ከማድረግ አንጻር አስተዋጽኦው ከፍ ያለ ነው። በዚህም በቀጣይ እንደ አይ.ሲ.ቲ እና ሌሎች ከጣቢያው ሥራ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ስልጠናዎችን ለተቋሙ ሠራተኞች የማመቻቸት እቅድ ተይዟልና ተግባራዊ ይደረጋል። በቀጣይ ሳምንት እትማችን ጣቢያው ማህራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንጻር ያከናወናቸውን ተግባራት በተመለከተ እንደምናስነብባችሁ ከወዲሁ ቃል እየገባን ተሰናበትን።